የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት
Road Safety & Insurance Fund Service

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር

# የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት

# በጥፋት ምክንያት የብቃት ማረጋገጫቸው ለታገደባቸው አሽከርካሪዎች የተዘጋጀ የተሃድሶ ሥልጠና አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር ---------/2017"

መስከረም/ 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መመሪያ ቁጥር --------2017

## በጥፋት ምክንያት የብቃት ማረጋገጫቸው የታገደባቸው አሽከርካሪዎች የተሐድሶ ሥልጠና አሰጣጥ መመሪያ

**መግቢያ**

ሁሉንም ተሽከርካሪዎች በሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች አማካኝነት የሚደርሰው የትራፊክ አደጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና ብዙዎችን ለህልፈተ ሕይወትና ለአካል ጉዳት እንዲሁም ለከፍተኛ የንብረት ውድመት እየዳረገ የሚገኝ ክስተት በመሆኑ በሀገራችንም ሆነ በአለም አቀፍ የሚደርሱ አደጋዎች በአሽከርካሪው ስህተት እንደሆነ ሪፖርቶች ያሳያሉ።

ለትራፊክ አደጋ መከሰት የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም በዋናነት ግን የአሽከርካሪዎች ስህተት ከፍተኛውን ድርሻ ስለሚይዝ እና በጥፋት ምክንያት ከታገዱ በኃላ ዳግም ወደ ስራ ለመመለስ የተሐድሶ ስልጠና በማስፈለጉ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 አንቀጽ 12(2) እና በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 አንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 6 (ለ) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።በተጨማሪም የትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 557/2016 አንቀጽ96 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ተደጋጋሚ ጥፋት አጥፍተው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋጋጫ ፍቃዳቸው የታገደባቸው አሽከርካሪዎች ጥፋታቸውን ሊያርም በሚያስችል መልኩ እውቀትና ክህሎት መሰረት ያደረገ የተሐድሶ ስልጠና ወስደው ወደ ስራ እንዲመለሱ ለማስቻል መመሪያውን ለማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የአጥፊ አሽከርካሪዎች የተሐድሶ ሥልጠና አሰጣጥ_**መመሪያ ቁጥር**--------/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1) **"ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር"** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት ነው።

2) **"አገልግሎት"** ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 493/2014 መሠረት የተቋቋመው የመንገድ ደኅንነት እና የመድን ፈንድ አገልግሎት ነው።

3) **"አሽከርካሪ"** ማለት ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የሕዝብ እና የጭነት ማመላለሽ ተሽከርካሪዎችን የሚያሽከረክር ሰው ነው።

4) **"የተሐድሶ ስልጠና ማለት"** ማለት በደንበ ቁጥር 557/ 2016 አንቀጽ96 ንኡስ እነቀጽ1 መሰረት የሚሰጥ በጥፋታቸው ምክንያት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫቸው ለታገደባቸው አሽከርካሪዎች ሚሰጥ የዕወቀትና ክህሎት ስልጠና ነው።

5) **"መደበኛ ሥልጠና"** ማለት በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 አንቀጽ 2(41) መሠረት የሚሰጥ የሥልጠና ዓይነት ነው።

6) " **የሥልጠና ሰነድ"** ማለት **የተሐድሶ** ሥልጠና ለሚሰጣቸው አሽከርካሪዎች በተቀመጠው ርዕስ ላይ በአገልግሎቱ የጸደቀ ለማስተማሪያነት የሚዘጋጅ ሰነድ ነው።

7) **"አሠልጣኝ"** ማለት በማሽከርከር ብቃት ሥልጠና ለመስጠት የሙያ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው።

8) **"ማሠልጠኛ ተቋም"** ማለት በማሽከርከር ብቃት ሥልጠና ለመስጠት በሕግ እውቅና ያለው መንግሥታዊ ወይም የግል የአሽከርካሪ ማሠልጠኛ ተቋም ማለት ነው።

9) **"ቢሮ"** ማለት የመንገድ ትራንስፖርትን ለመምራት ሥልጣን የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ነው።

10) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰዉነት ችሎታ የተሰጠዉ ነው፤

11) በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 እና በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 እና በደንበ ቁጥር 557/ 2016 የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደ የአግባብነታቸው ለዚህ መመሪም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

12) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አገላለፅ ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>ዓላማ</u>

አሽከርካሪዎች የተሐድሶ ሥልጠና በመስጠት ተደጋጋሚ ከሚፈጽሟቸው ስህተተቶች በማረም እንደሁም እውቀታቸውንና ክህሎታቸውን በማሳደግ ብቁ እንዲሆኑ በማድረግ የሚደርሰውን የሞት፣ የከባድ እና ቀላል የአካል ጉዳት፣ እንዲሁም ከፍተኛ የንብረት ውድመትን መቀነስ ነው።

4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የብቃት ማረጋጋጫ ፈቃዳቸው ተደጋጋሚ በሚፈጽሟቸው ጥፋቶች ምክንያት የታገደባቸው አሽከርካሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## የተሐድሶ ሥልጠና አሰጣጥ ድጋፍ ማዕቀፎች

5. **የተሐድሶ ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችል የድጋፍ ማዕቀፍ**

1) **የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመሆን፡-**

   ሀ) መመሪያው አጥፊ አሽከርካሪዎች ላይ ወጥነት ባለው መንገድ እየተፈጸመ መሆኑን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

   ለ) የመመሪያውን አተገባበር ውጤታማ ለማድረግ ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ድጋፍ ያደርጋል፤ ያስተባብራል፤

   ሐ) ሀገር አቀፍ የተሐድሶ ሥልጠና ሰነዶች በአገልግሎቱ ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት ያጸድቃል፤

   መ) የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ በአገልግሎቱ ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት መርምሮ ያጸድቃል፤

   ሠ) የመመሪያውን አፈጻጸም በመገምገም የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

2) **የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ ከሆኑና ማንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመሆን፡-**

ሀ) በመመሪያው አተገባበር ዙሪያ ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለተለያዩ አካላት ግንዛቤ ያስጨብጣል።

ለ) የሥልጠና ሰነድ በማዘጋጀት እንዲፀድቅ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል።

ሐ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሥልጠና ሰነዱን ይዘት በመፈተሽ የማስተካከያ ሐሳብ ያቀርባል።

መ) አጠቃላይ ሥልጠናው ስለሚሰጥበት አግባብ የሥልጠና መርሀ-ግብር ያወጣል፤ በወጣው መርሀ-ግብር መሠረት መፈፀሙንም ይከታተላል።

ሠ) የተሐድሶ ሥልጠና የሚሰጡ ተቋማት ሥልጠናውን የሚሰጡበትን መስፈርት ያዘጋጃል።

ረ) የተሐድሶ ሥልጠና የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል።

ሰ) የተሐድሶ ሥልጠና ሰርቲፊኬት ያዘጋጃል፤ ሥልጠናውን ለሚሰጡ አካላትም ያሰራጫል።

ሸ) በሀገር አቀፍ ደረጃ ሥልጠና የሰጡ ተቋማት መረጃን በአግባቡ ያደራጃል፤ በየጊዜው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል።

ቀ) የተሐድሶ ሥልጠናው አሰጣጥ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች በጣሱ አሠልጣኞች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል።

በ) በፌደራል ደረጃ ሥልጠና ለመስጠት ፈቃድ ለሚጠይቁ ፍቃድ ይሰጣል፣ የተፈቀደላቸውን አካላት የፈቃድ ዕድሳት ጊዜን ይወስናል።

ረ) የተሀድሶ ስልጠና ለወሰዱ አሽከርካሪዎች ፈተና ማዘጋጀትና የመፈተን ውጤቱንም ስልጠና ለወሰዱበት ተቋም ማሳወቅ

3) **የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ ከሆኑና ማንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመሆኑ-**

በክልሉ ሕግ የተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ተከታዮቹን ሥራዎች ያከናውናል።

ሀ) ይህን መመሪያ የመፈፀምና የማስፈፀም፤

ለ) በመመሪያ አተገባበር ላይ ለተለያዩ አካላት ግንዛቤ የማስጨበጥ፤

ሐ) የተሐድሶ ሥልጠና የሚሰጡ አካላትን በወጣዉ ስታንዳርድ ወይም መስፈርት መሠረት በመለየት ለአገልግሎቱ የማሳወቅ፤

መ) በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚታተመዉን የተሐድሶ ሥልጠና ሰርተፍኬት ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል ለሰልጣኞች ይሰጣል፤

ረ) የሥልጠናዉን አፈጻጸም ለመከታተል በየደረጃዉ ባለዉ መዋቅር የድጋፍ፤ ክትትልና ቁጥጥር ሥራ ያከናዉናል፤

ሰ) በክትትልና ቁጥጥር የተገኙትን የአፈፃፀም መረጃዎች ለአገልግሎቱ ሪፖርት ያደርጋሉ፤

ረ) የተሀድሶ ስልጠና ለወሰዱ አሽከርካሪዎች ፈተና ማዘጋጀትና የመፈተን ውጤቱንም ስልጠና ለወሰዱበት ተቋም ማሳወቅ

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ግዴታዎች</u>

### 6. የተሐድሶ ሥልጠና የሚሰጡ ተቋማት ግዴታዎች

የተሐድሶ ሥልጠና ለመስጠት ፈቃድ የተሰጠው ተቋም የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል።

ሀ) የተሐድሶ ሥልጠና የሚወስዱ አሽከርካሪዎችን ስም ዝርዝር፤ የሥልጠና መርሀ-ግብር ለአገልግሎቱ የማሳወቅ፤

ለ) ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መስፈርት መሠረት የተሐድሶ ሥልጠና መስጠት የሚያስችል የሙያ ፈቃድ የመያዝ፤

ሐ) ሚኒስቴሩ በሚያወጣው የተሐድሶ ሥልጠና ሰነድ መሠረት የተሐድሶ ሥልጠና መስጠት፤

### 7. የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ማህበር ግዴታዎች

ማንኛውም ተሽከርካሪ ባለቤት የሚቀጥረው አሽከርካሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫው በተደጋጋሚ ጥፋት ምክንያት ያልታገደ መሆኑ ወይም ካሁን ቀደም የታገደ ከሆነ ደግሞ የተሐድሶ ስልጠና ስልጠና ሰርቲፊኬት መያዙን የማረጋጋጥ ግዴታዎች አሉበት።

ሀ) በዚህ መመሪያ መሰረት የሚቀጥራቸው አሽከርካሪዎች ካሁን ቀደም በጥፋት በምክንያት የታገዱ ከሆኑ የተሐድሶ ስልጠና ሰርቲፊኬት መያዛቸውን የማረጋጋጥ

ለ) ለአሽከርካሪዎች የተሐድሶ ስልጠና በሚሰጣቸው ጊዜ የማስተባበር፤ የመከታተል እና የመደገፍ፤

ሐ) በማህበሩ ሥር የሚገኙ አሽከራካሪዎች የጥፋት ነጥባቸውን በመከታተል በወቅቱ የተሐድሶ ሥልጠና እንዲያገኙ የማስተባበር፤

### 8. የአሽከርካሪዎች ግዴታዎች

ማንኛውም የአሽከርካሪ ብቀቃት ማረጋጋጫ የታገደበት አሽከርካሪ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡፡

ሀ) ማንኛውም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋጋጫ የታገደበት አሽከርካሪ የተሐድሶ  ሥልጠና ሰርተፍኬት መውሰድ አለበት

ለ) የተሐድሶ  ሥልጠና ለመውሰድ ወደ ማሠልጠኛ ተቋም በሚሄድበት ጊዜ  የታገደበት እና እግዱን ስለማጠናቀቁ ማስረጃ  ይዞ የመገኘት፤

ሐ) ሥልጠናውን ከመውሰዱ በፊት ማሟላት የሚገባውን አስገዳጅ ሁኔታዎችን በመፈጸም ሕጋዊ ማስረጃ ይዞ የመቅረብ ወይም ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልቶ የመገኘት፤

መ) የተሐድሶ  ሥልጠና ከወሰደ በኃላ የሚሰጠውን ፈተና የማለፍ ግዴታ

## ክፍል አራት

## ስለ የተሐድሶ  ሥልጠና ይዘትና ሥልጠናው ስለሚሰጥበት አግባብ

### 9. የተሐድሶ  ሥልጠና ሰነድ ይዘት

1) የመንገድ ትራፊክ አደጋ ነባራዊ ሁኔታዎች፤
2) የመንገድ ትራፊክ አደጋ መንስኤዎች እና መከላከያ መንገዶች፤
3) የማሽከርከር ሥነ- ባህሪ፤
4) ሙያዊ ሥነ-ምግባር
5) የመልካም አሽከርካሪ ባህርያትን ለማዳበር የሚጠቅሙ አካላዊ እና ሥነ- ልቦናዊ እውነታዎች፤
6) አደጋን ተከላክሎ ማሽከርከር፤
7) የፍጥነት መንገድ አጠቃቀም
8) የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እርዳታ፤
9) የተሐድሶ  ሥልጠና የሚሰጥበት መንገድ በፓወር ፖይንት፣ የቡድን ውይይት በማድረግ፣ አስታማሪ በሆኑ ቪዲዮዎች፣ በፎቶ ግራፎች እና መሰል የማስተማሪያ ዘዴዎች ይሆንል፡፡
10) በሲሙለተር  የተግባር የመንገድ ስነስርዓትና  የአነዳድ ልምምድ ማድረግ

### 10. የተሐድሶ ሥልጠናውን የሚሰጡ አካላት

የተሐድሶ  ሥልጠናውን የሚሰጡት አገልግሎቱ በሚያወጣው የተሐድሶ  ሥልጠና መስጫ መመዘኛ መስፈርት መሠረት የተሐድሶ  ሥልጠናውን ለመስጠት ፈቃድ  የተሰጣቸው አካላት ይሆናሉ፡፡

11. የተሐድሶ  ሥልጠናውን ለመስጠት ፈቃድ የሚሰጣቸው አካላት ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤

1) በዘርፉ በቂ እውቀትና ልምድ ያለው፤
2) ከክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ የተሐድሶ  ሥልጠና ለመስጠት ፈቃድ የተሰጠው፤

3) ለሥልጠና ምቹ የሆነ የሥልጠና ክፍል እና ቁሳቁሶችን የሚያሟላ ሆኖ በመስፈርቱ መሰረት የተጠቀሱትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፡፡

## 12. የተሐድሶ ሥልጠናውን ለመስጠት ፈቃድ የሚሰጣቸው ተቋማት ግዴታዎች

የተሐድሶ ሥልጠናውን ለመስጠት የሚያስችል የሙያ ፈቃድ የተሰጠው ተቋም የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡፡

1) አስፈላጊውን መስፈርት በማሟላት የተሐድሶ ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችል ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የሙያ ፈቃድ የመያዝ፤
2) የተሐድሶ ሥልጠና ሰጪነት ፈቃድ በየዓመቱ የማሳደስ፤
3) በየጊዜው ሥልጠና የሚሰጣቸውን አሽከርካሪዎች ብዛትና ልዩ ልዩ መረጃዎች ለፈቃድ ሰጪው ሪፖርት የማድረግ፤
4) ተቋሙ ወይም ድርጅቱ የተሐድሶ ሥልጠናውን መስጠት ካቆመ ወይም የተቀመጡትን ግዴታዎች መወጣት ካልቻለ ለፈቃድ ሰጪው አካል ፍቃዱን የመመለስ፤

## 13. ስለ ሥልጠና ጊዜ

1) የተሐድሶ ሥልጠናውን ሲወስድ በቀን 2 ሰዓት ሆኖ ለ7ቀን 14 ሰዓታት በክፍሉ ውስጥ ተገኝቶ ሥልጠናን መውሰድ አለበት፡፡

## 14. ስለ ሥልጠና ወጪ

የተሐድሶ ስልጠና የሚወስዱ አሽከርካሪዎች አገልግሎቱ በሚያወጣው የታሪፍ ስሌት መሠረት በራሱ በሰልጣኙ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

# ክፍል አምስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 15. ክልከላ

1) በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት ማንኛውም በፈጸማቸው የማሽከርከር ስህተት የማሽከርከር ብቃት ፍቃዱ የታገደበት አሽከርካሪ የተሐድሶ ሥልጠና ሳይወስድና ሰርተፊኬት ሳይዝ ማሽከርከር የተከለከለ ነው፡፡
2) ማንኛዉም የተሽከራካሪ ባለቤት ተሽከርካሪውን በፈጸማቸው የማሽከርከር ስህተት የማስከርከር ብቃት ፍቃዱ የታገደበት አሽከርካሪ የተሐድሶ ሥልጠና ያልወሰደና የተሐድሶ ሥልጠናውን ስለ መውሰዱ የሚያረጋግጥ ሰርቲፊኬት ያልያዘ አሽከራካሪ እንዲያሽከረክር መፍቀድ የለበትም፡፡
3) የተሐድሶ ሥልጠና ለማሠልጠን የሚያስችል ፈቃድ የተሰጠው ተቋም ፈቃዱን ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

## 16. አስተዳደራዊ እርምጃዎች

በሌሎች ሕጎች የተቀመጡ ቅጣቶች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

1) የተሐድሶ ሥልጠና ላልወሰደ አዋሬ አሽከሪካሪ መንጃ ፍቃዱን የሰጠ አካል ወይም የፈቀደ በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ መሠረት የሚቀጣ ሲሆን አሽከርካሪው ከማንኛዉም የማሽከርከር አገልግሎት ለ 3 ወራት ዳግም ይታገዳል።
2) በዚህ መመሪያ መሠረት ኃላፊነት የተጣለበት ማንኛውም የማሠልጠኛ ተቋም የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ ለመጀመሪያ ጊዜ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣ ለሁለተኛ ጊዜ ለ6 ወር ይታገዳል፤ ከ3ኛ ጊዜ በላይ ከሆነ የሥልጠና ፈቀዱ ይሰረዛል።

17. ***የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት***

1) ማንኛውም ቅሬታ ያደረበት ግለሰብ ወይም ተቋም ቅሬታው በተፈጠረ በ7 የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው ቢሮ ማቅረብ ይችላል።
2) ቢሮው ቅሬታው በቀረበ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ ውሳኔውን ማሳወቅ አለበት።
3) ቢሮው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ግለሰብ ወይም ተቋም ውሳኔው በተሰጠ በ7 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬተውን ለትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ያቀርባል።
4) የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ቅሬታው በቀረበ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ ውሳኔውን ያሳውቃል።
5) የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻው አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል።

18. ***መመሪያውን ስለማሻሻል***

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሚኒስቴሩ ሊሻሻል ይችላል።

5.7. ***መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ***

ይህ መመሪያ ከ ----------------ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**ዶ/ር አለሙ ስሜ**

አባሪ 1

**የአሽከርካሪዎች የተሀድሶ ሥልጠና ማረጋጫ ምስክር ወረቀት**

የፈቃድ ሰጪ ስም------------------------

የአሽከርካሪ ሙሉ ስም ________________________________ ፎቶ

የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ደረጃ፡-_______________

የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ቁጥር፡-______________

የምስክር ወረቀት ቁጥር ______________________________

ምስክር ወረቀት የተሰጠበት ቀን ______________________

ፈቃድ ሰጪ አካል ፊርማ__________________